ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)
ትዴፓ የህዝቦች ድምፅ ነው!

የካቲት ፲፩ን አስመልክቶ ከትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ)
<u>የተሠጠ መግለጫ</u>

የካቲት ፲፩ ቀን 1967 ዓ/ም ማለት የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ መብቱ የሚከበርባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ትኖር ዘንድ፣ ህወሓት ፀረ-ደርግ እና መሠሎቹ ትጥቅ ትግል የጀመረበት ቀን ነበር። ለዚህ በጎ ዓላማ አያሌ ወጣቶች መስዋእት ሲሆኑ ህዝቡም ሠላምና ዕድገት አገኛለሁ በሚል እሳቤ ብዙ መከራ አሳልፏል። በጣም የሚያሳዝነው ግን ከግማሽ ምእተ ዓመት (ከ47 ዓመታት) በኋላ፣ የትግራይ ህዝብ መከራ ከያኔው ጊዜ ብሶበት ብቻ ሳይሆን በታሪኩ አጋጥሞት የማያውቀው ዙሪያ መለስ (ፖለቲካዊ፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ) ስብራት ውስጥ መግባቱ ነው።

ይኸንን መራራ ሀቅ ማገናዘብ ያልቻሉና የህዝቡን መከራ የማይሠማቸው የህወሓት አመራር እና ግልብ ተከታዮቻቸው «የካቲት ፲፩» የህዝቡን ጥያቄ የመለሠ አውደ ቀን አስመስሎ በማቅረብ ከበሮ ሲደልቁ፣ ሲጨፍሩ እና ሲያስጨፍሩ ይታያሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ የትግራይ ህዝብ ያለበት ሁኔታ አዕምሮ ላለው ሠው የሚያሳዝንና ልብ የሚያቆስል እንጂ ጭፈራ የሚያስወጣ ቅንጣት ታክል ምክንያት የለውም።

የትግራይ ወጣት ይኸ ነው ተብሎ በውል በማይታወቅ ዓላማ-ቢስ ጦርነት ተገዶ እየገባ እንደ ቅጠል እየረገፈ ይገኛል፤ ከአላማጣ እስከ ደብረሲና በየመንገዱ ወድቆ ያለው ቀባሪ ያጣ ሬሳ ዘግናኝ ነው። ይባስ ብሎም ወገኑ በሆነው የአፋርና የአማራ ህዝብ ላይ ተመሣሳይ መከራ እያደረሠ በህዝቦች መሀከል የጥላቻ ዘር እየበተነ ይገኛል። በዚህ አውድ ሆኖ ማዘናን በሰከነ መንፈስ ለአስከፊው ችግር መፍትሄ እንደመሻት፣ ህዝቡ የደላው ይመስል በማስገደድ በየአዳራሹ በጭፈራ መጠመድ እንደ እብደት የሚቆጠር ነው እንላለን።

ትዴፓ በትግራይ ህዝብ ላይ ብቻ ሳይሆን ወገናችን በሆነው የአማራና የአፋር ህዝብ ጭምርም እየደረሠ ያለውን መከራ ምንጩ የህወሓት አመራር እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። ይኸ ቡድን ለ27 ዓመታት ኢትዮጵያን በአምባገነንት ሲመራ፣ ትግራይን ብቻ ሳይሆን መላው ኢትዮጵያን የድህነት መቀመቅ የከተተ፣ ህዝቡ ባልረባ ምክንያት እርስ በራሱ እንዲጋጭ ከዛ አልፎም እንዲገዳደል ያደረገ፣ በስግብግብነትና በመሠሪነት የተካነ ጭራቸኑም መውገድ ያለበት ቡድን መሆኑ ይገነዘባል። ይኸ ቡድን እስካለ ድረስ ደግሞ የትግራይ ህዝብ በሀገሩ ኢትዮጵያ ሠላም አግኝቶና ተንቀሳቅሶ ሠርቶ መኖር የማይችልበት ደረጃ ደርሷል። ስለዚህ የትግራይ ህዝብ በሀገሩ ኢትዮጵያ እንደ ማንኛውም ዜጋ መብቱ ተከብሮለት ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ተስማምቶና ተደጋግፎ መኖር ከፈለገ ነቀርሳውን የህወሓት አመራር ማስወገድ የግድ ይለዋል።

ትዴፓ የካቲት ፲፩ን ሲዘክር፣ የትግሉ ቀዳሚ ዓላማ ምን እንደነበረና ለዚህ ዓላማ የተከፈለው መስዋእትነት ከንቱ ያስቀረውን የህወሓት አመራርን በመኮነን ብሎም እንዲወገድ በመታገልና ኢትዮጵያዊነቱን አስረግጦ ለሠላምና ለኢትዮጵያዊ አንድነት ያለውን የትግል ቁርጠኝነት በማደስ ነው።

የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ የሚኖርበትን ስርዓት እንመሠርታለን!

ድል ለመላው ኢትዮጵያ!

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 03፣ ፖፓሲኖስ ሕንፃ 3ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ